© ሜጋ አሣታሚ ድርጅት

Mega publishing Enterprise

ስልክ

Tel 11 18 25

113190

ፖስታ ሣ.ቁ. 12684

መጀመሪያ በ1979 ዓ.ም. ታተመ

ሁለተኛ በ1991 ዓ.ም. ታተመ

ሥዕሎች መጀመሪያ:- በሉቃስ አማረ

ተሻሽሎ የተሳለው

በጌታቸው ሙሊሳ

በመስፍን ኃ/ማርያም


# ተመሳስሎ ተለያይቶ



ፀሐይ ጠዋት ጠዋት በስተምሥራቅ ትወጣለች ።




ፀሐይ ማታ ማታ ወደ ምዕራብ ትጠልቃለች ።




በግ ጸጉር አለው ።



ዶሮ ላባ አላት




ፈረስ ይጋልባል ።




መኪና በመሬት ላይ ይሽከረከራል ።



ድንጋይ ጠጣር ነው ።




ውሃ ፈሳሽ ነው ።



በሬ አራት እግር አለው ።



ሰው ሁለት እግር አለው ።




ኤሊ ቀርፋፋ ነች




ጥንቸል በጣም ሯጭ ነች ።



መርከብ በባሕር ላይ ይንሳፈፋል ፡፡




ዓሳ በባሕር ውስጥ ይኖራል ፡፡




ወፎች በሰማይ ላይ ይበራሉ።


አውሮፕላን በሰማይ ላይ ይበራል።




በአንድ መንደር ውስጥ ዶጬ የሚባል ትንሽ ሰው ነበር። ለመንደሩ ሰዎች ጫማ ይሰፋል። በመንደሩ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጫማ ሲፈልጉ ወደ እሱ ነው የሚሄዱት። ዶጬ አዲስ ጫማ ይሰፋላቸዋል። አሮጌውንም ያድስላቸዋል።

አንድ ቀን አቶ ደፍጥጤ የሚባሉ በጣም ትልቅ ሰውዬ መጥተው ዶጬ ጫማ እንዲሰራ ላቸው ጠየቁት። "ጫማውን ሰፍተህ ስትጨርስ አንድ ዶሮና ስድስት ዕንቁላሎች እሰጥሃለሁ" አሉት። ዶጬም "እሺ" አለና የአቶ ደፍጥጤን ጫማ መስፋት ጀመረ።






አቶ ደፍጥጤ ከሰው ሁሉ የተለዩ በጣም ግዙፍ (ትልቅ) ሰው በመሆናቸው እግራቸ ውም በጣም ትልቅ ነው። ዶፎጩ ደግሞ በጣም ትንሽ ነው።የአቶ ደፍጥጤን ጫማ ለመስፋት ስለተቸገረ እግራ ቸው ላይ በመሰላል እየወጣ ነበር የሚሰፋላቸው። ቀን ቀን እየመጡ አጠገቡ ቁጭ ሲሉ ለት ቆዳውን በእግራቸው እየለካ ቶሎ ቶሎ ይሰፋል። ከብዙ ቀን በሁዋላ ለአቶ ደፍጥጤ የቀኝ እግር የሚሆን ትልቅ ጫማ ሰፍቶ ጨረሰ።




አቶ ደፍጥጤ ጫማውን ሲያዩ በጣም ደስ አላቸው።"ሁለተኛውን ጫማ ስፋልኝ። ቶሎ ከጨረስክልኝ ሌላ አራት ዕንቁላልና ሦስት የዶሮ ጫጩቶች እሰጥሃለሁ" አሉት። ዶጮ ግን "ቆዳ አለቀብኝ የርስዎ እግር በጣም ትልቅ ነው። አንዱ ጫማ ብቻ ለብዙ ሰው ጫማ የሚሆነኝን ቆዳና ሲባጎ ጨረሰብኝ" አለ።



አቶ ደፍጥጤም "ታዲያ ምን ይሻላል?" ብለው ጠየቁት። ዶጬ "ያለቀውን ያንድ እግር ጫማ ብቻ ይውሰዱና እርስዎ የፈለጉትን ይክፈሉኝ" አለ።

"ያንድ እግር ብቻ ምን ያደርግልኛል?" አሉና ተቆጡ።
"ያንዱን እግር ሌላ ጊዜ እሰፋልዎታለሁ" አለ ዶጬ።
አቶ ደፍጥጤም "አልፈልግም ለሌላ ሰው ሽጠው።"
ብለው ወደቤታቸው ሔዱ።



ዶጮም ትንሽ ካሰበ በኋላ ትልቁን ጫማ መኖሪያ ቤት ሊያደርገው ፈለገ።
በርና መስኮት፥ጣሪያ ሠራለት። ከዚያም ውስጡ ይኖር ጀመር።

## በሜጋ አሳታሚ ድርጅት የታተሙ
## የህፃ ት መጻሕፍት

| | | |
|---|---|---|
| * | የሰውነት ክፍሎች ........................................ | ብር 4.00 |
| * | የአማርኛ ፊደልና ቁጥር መማሪያ .......... | ብር 5.50 |
| * | ሥዕላዊ የሒሳብ መማሪያ ክፍል 1.......... | ብር 6.50 |
| * | » » » » 2............ | ብር 6.50 |
| * | ሙሽራዋ አይጥ ........................................ | ብር 3.40 |
| * | የፊደል ገበታ ........................................ | ብር 2.00 |
| * | ዕውዕዋይ (ትግርኛ) ........................................ | ብር 8.45 |
| * | The Alphabet........................................ | ብር 6.00 |
| * | Mega Primary English ............................. | ብር 3.75 |